በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 3.3.1/371/08
Ref. No
ቀን 11 መስከረም 2008
Date

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
ባሉበት፣

የዐቃቤ ህግ ቢሮ በቁጥር ዐ/ህ/ቢ.ሮ/739/07 በቀን 29/12/07 በተፃፈ ደብዳቤ የኮንተሮባንድ ዕቃ በሚያንገዙ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚሰጡ የውርስ ውሳኔዎችን በተመለከተ አስተያየትን ከህግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት በቁጥር ሕ/ም/አ/ዳ/244/07 በቀን 25/12/07 የተሰጠው የታመነበት መሆኑን በመግለጽ ለአፈፃፀም ልኳል።

በመሆኑም በተሰጠው የህግ አስተያየት መሠረት እንዲፈፀም እያሳሰብን፤ የህግ አስተያየቱን 3 ገጽ እና ሌሎች ተየያዥ የሆኑ 19 ገጽ አባሪዎችን አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

ማርታ ስዩም
የጉምሩክ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና
ክትትል ቡድን አስተተባባሪ

ግልባጭ፣
- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
  ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣



ስልክ ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ -ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

# ኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
# Ethiopian Revenues and Customs Authority
## የውስጥ ማስታወሻ
## Internal Office Memorandum

ለ፡- ሕግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር

ቀን ፡-29/12/07

ከ፡-ዐቃቤ ህግ ቢሮ

ቁጥር፡- ዐ/ህ/ቢሮ/739/07

ቀለሙ ቢያድግልኝ
የዐቃቤ ሕግ ቢሮ ኃላፊ
/ዋና ዐቃቤ ሀግ/

**ጉዳዩ፡- የኮንትሮባንድ ዕቃ በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚሰጡ የውርስ ውሳኔዎችን በተመለከተ የተሰጠ አስተያየት ስለመላክ፤**

የኮንትሮባንድ ዕቃ በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚሰጡ የውርስ ውሳኔዎችን በተመለከተ አስተያየት እንዲሰጥበት በቀን 18/12/07 በተመራልን መሠረት ከህግ አንፃር ለተጠየቀው አስተያየት ከሕግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት በቀን 25/12/07 በቁጥር ሕ/ም/አ/ዳ/244/07 በተፃፈ የውስጥ ማስታወሻ የተሰጠውን የሕግ አስተያየት ለዐቃቤ ህግ ቢሮ ኃላፊ ቀርቦ የታየ በኋላ የተሰጠው አስተያየት የታመነበት በመሆኑ የጥያቄውን መነሻ ዋናውን እና አስተያየቱን በድምሩ 21 ገፅ አያይዘን የላክን መሆኑን እየገለፅን የተሰጠው የሕግ አስተያየት በወጥነት ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ቢላክ የተሻለ ነው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

ከሠላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. 2
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

ኮ/ሥ/ገ/2137
18/12/07

ህ/ጽ/2272
18/12/07

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
# Ethiopian Revenues and Customs Authority
## የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
## የውስጥ ለውስጥ ማስታወሻ

ለ:- ለሕግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ

ቁጥር:- የጉ/ጉ/አ/አ/ቡድን 129/07

ከ: የጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ

ቀን:- 14/12/07

ም/ዋና ዳይሬክተር
የጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና
ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ

ጉዳዩ:- የኮንትሮባንድ ዕቃ በሚያጓጓዙ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚሰጡ የውርስ ውሳኔዎችን ይመለከታል።

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 153 (2) (ለ) መሠረት በዘርፋችን ውሳኔ ከሚሰጣቸው አቤቱታዎች መካከል አንዱ በማጓጓዣዎች ላይ በሚሰጥ የውርስ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ መሆኑ ይታወቃል። በዚህ መልኩ ከቀረቡት አቤቱታዎች መካከል በአብዛኞቹ ላይ በቅ/ጽ/ቤቶች ውሳኔ የተሰጠው በአዋጁ አንቀጽ 147 (3) (ለ) መሠረት ሲሆን ይህ የአዋጁ ድንጋጌ የማጓጓዣው ባለቤት እያወቀ የድርጊቱን መፈፀም ለመከላከል ወይም ለማስቆም ተገቢውን እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ ማጓጓዣው ውርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንደሚደረግ የሚገልፅ ነው። ነገር ግን በዚህ ረገድ ቅሬታ አቅራቢዎች እያነሱት ያለው ዋነኛ መከራከሪያ ተሽከርካሪውን የሚያስተዳድረው ወኪል በመሆኑ የድርጊቱን መፈፀም እነሱ እንደማያውቁ ወይም ሊያውቁ እንደማይችሉ እንዲሁም አዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 ከዚህ በፊት በስራ ላይ እንደነበረው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ባለቤት ወኪልን ይጨምራል የማይል መሆኑን ነው።

በመሆኑም በጽ/ቤታችን በኩል በእነዚህ ቅሬታዎች ላይ ተገቢውን የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ እንዲያስችለን ህገወጥ ዕቃ ጭነው በሚገኙ ማጓጓዣዎች ላይ በአዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀፅ 147 (3) (ለ) መሠረት ውሳኔ ለማስተላለፍ የድርጊቱን መፈፀም ወኪሉ እንደሚያውቅ ማረጋገጥ በቂ ነው ወይስ ባለቤቱም ያውቅ እንደነበር ማረጋገጥ ያስፈልጋል በሚለው ነጥብ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥበት እየጠየቅን ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ከቀረቡት አቤቱታዎች መካከል አንዱን የሚያሳይ 7 ገፅ አባሪ አድርገን ልከናል።

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ:-
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
  ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን

19/12/07

የሰማወቅለአማኅው-ነበረና!

ቀን 16/10/2007 ዓ.ም

*ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን*

*አቤቱታ አጣሪ ቡድን*

***አዲስ አበባ***

አመልካች .... አቶ ተስፋዬ ረታ ተሊላ

መልስ ሰጪ ... የኮምቦልቻ ገ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት

***በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 154 /1/ መሠረት የቀረበ ይግባኝ አቤቱታ***

***የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ***

የሰሌዳ ቁጥር ኮድ-3-49654 ንብረነቱ የአቶ ተስፋዬ ረታ ተሊላ የሆነ ኤፍ ኤስ አር /FSR/ የጭነት ተሽከርካሪ 4678 ኪ.ግ ሕገ ወጥ ልባሽ ጨርቅ በመጫን በጭፍራ መስመር ወደ ወልዲያ በመጓዝ ላይ ሣለ በደረሰበት የመገልበጥ አደጋ ከነ ሕገ-ወጥ እቃው ወድቆ የተገኘ ሲሆን ተሽከርካሪው ወደ ኮምቦልቻ ገ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት ተወስዶ አስፈላጊው ምርመራ ሲደረግ ከቆየ በኋላ በቀን 10/09/2007 ዓ.ም በቁጥር 5.0/2.1/0/9663 በቅ/ጽ/ቤቱ በተሰጠ ማስታወቂያ ተሽከርካሪው የተያዘበትን ምክንያት በመጥቀስ የተሽከርካሪው ሕጋዊ ወኪል ያለውን የውርስ መቃወሚያ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲያቀረብ ታዝዞ ወኪሉም በቀን 21/09/07 ያለውን ተቃውሞ አቅርቧል፡፡

ቅ/ጽ/ቤቱም ጉዳዩን በዚህ መልክ ሲመረምር ከቆየ በኋላ የተሽከርካሪውን ባለንብረት ስለተፈጸመው የኮንትሮባንድ ወንጀል መፈጸም በተገቢው መንገድ ሣያጣራ እና ሣይመዝን በደፈናው ወኪሉ መኪናው ወደ አፋር ክልል ከሰል ለመጫን መንቀሣቀሱን ያውቅ የነበረ በመሆኑ የመኪናውን ሥራ ስምሪት ያውቃል፡፡ ስለዚህ ስለተፈጸመው ወንጀል እውቀት ነበረው ያስብላል በማለት በመኪናው ሕጋዊ ባለቤት በኩል የቀረቡትን ሕጋዊ መቃወሚያዎች ከተፈጸመው ጉዳይ አንጻር ሣይመዝን በቀን 06/10/07 በቁጥር ካም.2/21/0/10647 በተጻፈ ደብዳቤ የተያዘበትን ተሽከርካሪ ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ የአሁኑም ይግባኝ የቀረበው ይህንኑ የውርስ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

***የአመልካች የቅሬታ ነጥቦች***

በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀጽ 147 መሠረት ባለቤት የሚለው ትርጓሜ ወኪልን የሚያካትት አለመሆኑን እና በወኪል አማካኝነት በተሰራ የጉምሩክ ወንጀል የንብረቱ ሕጋዊ ባለቤት እውቅና መኖሩን የማያሣይ አለመሆኑን፡፡

0921499751 - 0911386701

በአዋጅ ቁጥር 859/2006 በአንቀጽ 147 /3/ /ለ/ መሠረት በጉምሩክ ወንጀል ምክንያት ተሽከርካሪው ሊወረስ የሚገባው የንብረቱ ባለቤት እንዳወቀ የድርጊቱን መፈጸም ሣይከላከል የቀረ ከሆነ እንደሆነ ሕጉ በግልጽ ይደነግጋል። በዚህ ድንጋጌ ላይ መኪናውን ለመውረስ የመኪናው "ባለቤት" ማነው የሚለው ጉዳይ በቅድሚያ መታወቅ አለበት። በፍታብሄር ሕግ ባለቤት ማለት የሚለው በሕጉ አንቀጽ 1204 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያስረዳሉ።

ስለዚህ በፍትሀብሄር ሕግ እና በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ መሠረት ባለቤት ማለት የሚለው ትርጓሜ ተወካይን ወይም ወኪልና የሚያካትት አይደለም። አሁን ወደ ተያዘው ጉዳይ ስናመራ በኮንትሮባንድ ወንጀል ድርጊት የተያዘው የሰሌደ ቁጥር ኮድ-3-49654 አይሱዙ መኪና ሕጋዊ ባለቤት አቶ ተስፋዬ ረታ ተሊላ መሆናቸውን የመኪናዋ ስም ባለሀብት ወይም ሊብሬ ያሣያል። አቶ ብርሃኑ አሰፋ የሕጋዊ ባለቤቱ ወኪል እንጂ የመኪናው ባለቤት አይደሉም። ስለዚህ በወኪል አማካኝነት ባተፈጠረ የጉምሩክ ወንጀል ሕጋዊ የመኪናው ባለቤት ማለትም አቶ ተስፋዬ ረታ ተሊላ ስለ ድርጊቱ አፈጻጸም ምንም አይነት እውቀና ያልነበራቸው ሆኖ እያለ እንዲሁም የኮምቦልቻ ገ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት የመኪናው ባለቤት እውቀና የነበረው ስለመሆኑ አንዳችም ማስረጃ እና መረጃ ባላቀረበበት ሁኔታ በደፈናው የመኪናው ሕጋዊ ባለቤት ወኪል ስለ ድርጊቱ እውቅና ነበረው በማለት በደፈናው የንብረቱን ሕጋዊ ባለቤት እውቅና ሣያጣራ የውርስ ውሣኔ ትእዛዝ መስጠቱ የጉምሩክ ሕግን እንዲሁም ስለ ንብረት ባለቤትነት የሚደነግገውን መሠረታዊ የሕግ መርህ ያላገናዘበ ውሣኔ በመሆኑ ይህም ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ውሣኔው ሊሻር ይገባዋል። ከዚህም በላይ በወኪል አማካኝነት በተፈጠረ የወንጀል ድርጊት መኪናን የሚያክል ንብረት ስለ ወንጀል ድርጊቱ መፈጸም የንብረቱ ሕጋዊ ባለቤት እውቅና የነበረው መሆኑ ሣይረጋገጥ በደፈናው የውርስ ትእዛዝ መስጠቱ የጉምሩክ ሕግ አንቀጽ 147 /3/ /ለ/ ድንጋጌ ማለትም "ባለቤቱ እያወቀ" የሚለውን ትርጓሜ ወኪልን የሚያጠቃልል ባለመሆኑ የቅ/ጽ/ቤቱ የውርስ ውሣኔ ትእዛዝ የሕግ መሠረት የለውም በመባል አመልካች የተያዘብኝን መኪና እንዲለቀቅብኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

## 2/ የመኪናው ሕጋዊ ባለቤት ወኪል ወይም ተወካይ ስለፈጸመው የኮንትሮባንድ ወንጀል ድርጊት እውቅና ያልነበረው ስለመሆኑ፡-

- በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ መሠረት የሚወረሱ እቃዎችን ለማጓጓዝ የዋለ ማጓጓዣ የሚወረስባቸው ሁኔታዎች በአዋጁ አንቀጽ 147 /3/ ላይ በዝርዝር የተመለከቱ ሲሆን በዚህ አንቀጽ 3 /ለ/ ላይ የሚጓጓዘው ባለቤት እያወቀ የድርጊቱን መፈጸም እርምጃ ሣይወስድ ከቀረ ማጓጓዣው የሚቀር ለመሆኑ ተመልክቷል። ሆኖም ግን በዚህ ጉዳይ ተወካዩ የንብረቱ ወኪል እንጂ የንብረቱ ባለቤት ባለመሆኑ እና የወኪሉ ስለ ድርጊቱ መፈጸም ያለው እውቀት የንብረቱ ባለቤት እንዳወቀ

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation

የሚያስቶጥረው አይደለም። ምክንያቱም በውክልና የመጣ ስልጣን የንብረቱ ባለቤት ሲያደርግ የማይችል ባለመሆኑ ውርሱ ተቀባይነት የለውም። ከዚህም በተጨማሪ የንብርቱ ሕጋዊ ወኪል ስለወንጀል ድርጊቱ አፈጻጸም እንዳችም እውቀት አልነበረው ለዚህም ማሣያ የሚከተሉት ፍሬ ጉዳዮች ያረጋግጣሉ።

- ❖ በመሠረቱ የኮንትሮባንድ ወንጀሉ በተፈጸመበት ቀን ወኪሉ መኪናው የከሰል ንግድ እየሰራ የነበረ መሆኑን እንጂ እንደዚህ አይነት ተግባር ውስጥ መኖሩን አላውቅም። እኔ ወኪል በውክልና የተሰጠኝ መኪና የስራ ስምሪት የሰጠሁት ለአቶ አበባው ጥላሁን ለተባለ ግለሰብ ነው። ይህም ግለሰብ በተሰጠው ስራ የከሰል ንግድ እየሰራ የነበረ ቢሆንም ግለሰቡ ባጋጠመው የጤና ችግር ምክንያት አቶ ጀማል የሚባል ሹፌር ተክቶ እንዲሰራ ተደርጓል። ከዚህም በላይ በወቅቱ ከሰሉ መልካ ወረር አካባቢ በተነሣው የጎሣ ግጭት ምክንያት ከሰል መጫን ባለመቻሉ ለ7 ቀን ቆሞ የነበረ መሆኑን አውቃለሁ። ከዚህ በኋላ አፋር ክልል ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የከሰል ሽያጭ የሚከናውን በመሆኑ መኪናውም ከሌላ ቦታ ከሰል ለመጫን መንቀሣቀስ እንዳለበት ከአዲሱ ሹፌር ጋር በመነጋገር የሥራ ስምሪት ተሰጥቶታል። ማንም ሰው እንደሚያደርገው መኪናው ጭነት ወዳለበት ቦታ መንቀሣቀሱ ወንጀልነት የለውም። ከዚህ በላይ ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜም ይሁን በኋላ እኔ አዳማ ከተማ የነበርሁ መሆኑ የሚገልጽ የማህበራዊ ፍ/ቤት በምስክሮች በማረጋገጥ ማስረጃ ተጥቶል። ከዚህም በላይ መኪናው የተያዘው በራሱ ሰዓት ተገልብጦ ሲሆን መኪናው መገልበጡንም የሰማሁት በሌላ ቀን በሌላ ሰው አማካኝነት ነው። እኔ ወኪል ይህን አቤቱታ ሰሚ የማሣስበው ከሹፌሩ ጋር የኮንትሮባንድ ስራውን እየሰራሁ ቢሆን ኖሮ የመኪናውን መገልበጥ የዛኑ ቀን ማወቅ እችል ነበር። ነገር ግን ከዚህ ሹፌር ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለኝ እና ትእዛዝም ያልሰጠሁት መሆኑን ከላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ያስረዳሉ።

*3/ ቅ/ቤቱ መኪናው ውርስ እንዲሆን መሠረት ያደረጋቸው ፍሬ ጉዳዮች ባለቤቱ እውቀና የነበረው ስለመሆኑ እና የወኪሉ ስለ ተፈጸመው ወንጀል እውቀና ነበረው ለማለት የሚያስችሉ አለመሆናቸውን።*

- በመሠረቱ የመኪናው ውርስ ሲፈጸም በቅድሚያ ወራሹ አካል ስለ ድርጊቱ አፈጻጸም ሁኔታ እና ስለ ባለንብረቱ የወንጀል ድርጊት እውቅና በሚገባ ማረጋገጥ ሕግ ግድ የሚለው አሰራር ነው። አሁን ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ ቅ/ጽ/ቤቱ ወኪል በሕጋዊ መንገድ የመኪና ስምሪት ስራውን የሰጡት ግለሰብ የታመመ በመሆኑ ለማያውቁት ሰው አሳልፈው በመስጠት ይህን ድርጊት እንደፈጸሙ ያስረዳል በተጨማሪም ማንም ሰው ለማያውቀው ሰው ምንም ማስረጃ ሣይዝ ወይም

የመንጃ ፈቃድ ሣይዝ አሽከርካሪውን ይሰጣል ተብሎ አይገመትም በማለት ነው በመሠረቱ የቅ/ጽ/ቤቱ እነዚህ ምክንያቶች በመጥቀስ መኪናው እንዲወረስ አያስችሉም። እዚህ ጋር ይህ ጉባኤ እንዲያይልኝ የምፈልገው መኪናው የስራ ስምሪት የተሰጠው ከሠል ለመጫን እንጂ ኮንትሮባንድ ወንጀል ለመስራት አይደለም። ያዥ አካልም ወኪል መኪናውን የስምሪት ትእዛዝ ሰጥተሀል ከማለት ውጪ መኪናው ለምን አላማ ተሰማራ ማለትም ኮንትሮባንድ ለመጫን የነበረ መሆኑን አላረጋገጠም። እንደውም መኪናው ለ7 ቀን አዋሽ ሰባት ኪሎ ከሰል የሚጫን ያልነበረ በመሆኑ መቆቱ እንዲሁም ከዚህ በኋላ ሌላ ከሰል አለበት ከተባለው ቦታ ከሰል ለማውጣት መንቀሣሱ ወኪል መኪናውን በእንደዚህ አይነት ወንጀል አሰማርቶት ያልነበረ መሆኑን በተዘዋዋሪ የሚያስረዱ እውነታዎች ናቸው።

*4/ ካለ ምንም የጉምሩክ ቁጥጥር በራሱ ጊዜ ተገልብጦ በተገኘ ሕገ ወጥ እቃ ላይ ባለቤት እውቅና ነበረው በማለት ወራሽ አካል እውቅና መኖሩን የማስረዳት ሸክም ያለበት መሆኑን እና ይህን ሣያረጋግጥ በደፈናው ተሽከርካሪው ሙሉ የኮንትሮባን እቃ ብቻ በመጫኑ ውርስ ነው ማለቱ ተገቢ አለመሆኑን፡፡*

- ወራሽ አካል ተሽከርካሪውን ይወረሣል ሲል የመኪናው ባለቤት እቃውን ወደ ሚወሰድበት አካባቢ መኪናው ባዶውን ተጉዞ የነበረ መሆኑን ሕገ ወጥ እቃውም ከየት እንደተጫነ አላረጋገጠም። ሆኖም ግን አመልካች መኪናው የከሰል ጭነት እየሰራ እያለ እየጫነ መሆኑን በምስክሮች ማስረዳት እችላለሁ። ከዚህም ባለፈ ቅ/ጽ/ቤቱ አመልካች ለተጫነው ሕገ ወጥ እቃ የመኪና ኪራይ የተቀበልሁ መሆኑን ሣያረጋግጥ በደፈናው ታውቅ ነበር ማለቱ አግባብነት የለውም።

እንደውም አመልካች የከሰል ስራውን በሹፌር ሲያሰራ ሁልጊዜ አስቀድሞ የመኪና ኪራይ የሚቀበል ሲሆን መኪናው በተያዘበት ወቅትም ለከሰሉ ጭነት አስቀድሞ የማይቀበል ሲሆን መኪናው ከሰሉን በሚጭነት ቦታዎች ሁሉ አብሮ እየተንቀሣቀስ የመቆጣጠር ግዴታ የለበትም ምክንያቱም የአመልካች ቋሚ መኖሪያው አዳማ በመሆኑ ነው። በወቅቱ ወንጀሉ ሲሰራም አዳማ የነበረው መሆኑን በማስረጃ አረጋግጫለሁ። ከዚህም በላይ በወቅቱ መኪናዋን ሲያሽከረክር ከነበረው ግለሰብ ጋር ምንም አይነት የስልክ ግንኙነት የሆነ የጽሁፍ መልእክት አድርገን የማናውቅ ሲሆን ወንጀሉ ከተፈጸመ በኋላ እንዲሁ ምንም አይነተ ግንኙነት የለንም። በአጠቃላይ የኮንትሮባንድ ወንጀሉ ከፈጸመው ግለሰብ ጋር ለመመሣጠር የኮንትሮባድ ስራ ልንሰራ ይቅርና ለአንድ ጊዜም ቢሆን በአካል ቁጭ ብለን ተነጋግረን የማናውቅ ሰዎች ነን ለዚህም ማስረጃ በምስክሮች አረጋግጣለሁ።

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

በአጠቃላይ የኮምቦልቻ ገ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት አንድ ተሽከርካሪ ላይ ሙሉ የኮንትሮባንድ እቃ መጫኑ ባለቤቱ ድርጊቱን ያውቀው ነበረ ለማለት ወኪል ስምሪት ሰጥቶ ነበር በማለት በተገቢው ሁኔታ ሣያረጋግጥ እና በሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎች ሣያስደግፍ የውርስ ውሣኔ ትእዛዝ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ውሣኔው ተሽሮ መኪናዬ እንዲለቀቅ ትእዛዝ እንዲሰጥልኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

## ማስረጃዎች

### ሀ/ የሰው ማስረጃ

1. አመልካች ተሽከርከሪውን ለክሰል ስራ ጭነት እንዲውል የስራ ስምሪት ለሹፌር አቶ አበባው ጥላሁን በሀላፊነት ሰጥቼ ቀጥሬ እያሰራሁ የነበረ መሆኑን የሚያስረዱ ምስክሮች 1/ አቶ ደምስ ታደሰ 2/ አቶ ተስፋዬ በድሉ 3/ አቶ ተስፋዬ ክብሮም ናቸው።
2. አመልካች በወኪልነት የሚያስተዳድረው መኪና በደረሰበት የመገልበጥ አደጋ ወድቆ የሚገኝ መሆኑን ያወቅሁት በመኪናው አሽከርካሪ ሣይሆን በሌላ 3ኛ ወገን አማካኝነት በመሆኑን የሚያስረዳ የሰው ምስክር፡- አቶ ኃ/ስላሴ በርሄ ነው።
3. መኪናው የከሰል ጭነት ለመስራት ወደ ሰመራ ተንቀሣቅሶ የነበረው መሆኑን የሚያስረዱ የሰው ምስክሮች፡- 1/ አቶ ሀብታሙ በርሄ 2/ አቶ ሰይድ ሲሣይ 3/ አቶ ሞላ ደሣለኝ ናቸው።

### ለ/ የሰነድ ማስረጃ

1. የሰሌዳ ቀጥር ኮድ 3-49654 ኤፍኤስአር መኪና ሕጋዊ ባለቤትነት የሚገልጽ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር በአቶ ተስፋዬ ረታ ተሊላ ባለቤትነት መሆኑ እንጂ በአሁኑ አመልካች አቶ ብርሃኑ አሰፋ ባለቤትነት ያልተመዘገብ ስለመሆኑ የሚገልጽ የሰነድ ማስረጃ 03 ገጽ
2. የኮንትሮባንድ ወንጀሉ በተፈጸመበት ወቅት አመልካች በቦታው ያልነበረ እና በአዳማ ከተማ ከቀን 12/08/07 እስከ 18/08/07 ዓ.ም የነበረ መሆኑን የሚገልጽ የማህበራዊ ፍ/ቤት ውሣኔ 03 ገጽ በአባሪነት አያይዤ አቅርቤአለሁ።

አመልካች ሕ/ወ/ብርሃኑ አሰፋ

ብርሃኑ አሰፋ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. ፪
Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

Guyyaa.19/03/2007 ALH

**Waajjira Haqaa Godina Magaalaa Adaamaattii**
**Adeemsa Hojii Galmeessaa Ragaalee fi keennaa Hayyamaa tiif**
**ADAAMAA.**

**Ragaa aangoo bakka bu'uummaa.**

Bakka Bufatoon............1. Obbo Tasfaayee Rattaa Taliilaa

2. Aaddee Warqinash Dastaa

Teessoon Godina Arsii

**Bakka bu'aan...............Obbo Birihaanu Asaffaa Mahaarii**

**Teessoon M/Adaamaa , Ganda 01 , Lakk.Mana.2799**

Nuti keenniitota aangoo bakka bu'uummaan dhiirsaaf niitii seera qabeessaa yammu taanuu bakka buu'aadhaaf aangoo bakka bu'ummaa isaaf keenninuu **Maqaa bakka bufataa 1ffaa Obbo Tasfaayee Rattaa Taliilaatiin** galmaa'ee argamuu Lakk.Gabatee **3-49654 AA ,** Lakk.Shaansii **JALK6A13X87101425 , Lakk.Motoraa 6HE'L-435323** kan ta'ee konkolaataa Fe'iisaa Googaa keenyaa bakka bu'aa akka keenyaa ta'uudhaan konkolaataa kana akka bulchuu , akka to'atuu, akka eeguu , akka kireessuu , mallaqaa kiraa akka fudhatuu , Galii konkolaatichaa wal-heereegee akka fudhatuu , akka gurguruu , akka geeddaruu , maqaa akka jijjiiruu, mallaqaa akka fudhatuu , billeetaa akka keennuu fi akka fudhatuu , bolloo fi kalawudoo akka gosiisuu , gibirii fi kafaltii barbaachisaa ta'ee akka kafaluu , galmee akka sochaa'uu , ahaadii inshuraansii akka raawwatuu , heyyamaa daldalaa akka baasuu , akka haroomisuu , akka deebiisuu , konkolaachisaa akka qaxaruu akka geegeesuu , Diisipaach akka fudhatuu , Cheekii akka sharafamuu , dhimma nutii raawwachuu qabinuu kamiyyuu karaa dhaabbolee ummataatiis ta'ee waajjiraalee motummaa kamiyuuttii , Waajjiraa Gandichaattii fi Waajjiraa karaa geejiibaatti dhiyaachudhaan akka raawwatuu fi nuuf raawwachiisuu nama 3ffaa kan biraa YKN Abukaatoo Seeraa akka bakka busuu, akka diiguu bu'uura **S/H/H/Lakk. 2199 , 2204 fi 2205** ttii aangoo bakka bu'uummaa guutuu keennuu keenya mallattoo keenyaan ni mirkaneessina.

**Mallaattoo bakka bufatootaa**

1. [signature]
2. [signature]

Masrat Tiksee Tuchii
መሠረት ቲክሴ ቱቺ
Abbaa Alangaa Godinaa
Koppii Hafaa Intala Tembeenii
Qar.- 3-4 - Maxanfameera

ስታዲየም የትርጉም ሥራ አገልግሎት
Stadium Translation Service
T`ajaajila Turjumaana Istaadiyeemii
+25-115-15 81 30 +251-911-66 29 17 +251-930 09 83 02 10128, Email- stadiumtranslation@gmail.com Addis Ababa, Ethiopia

**አርማ**
**በአዳማ ከተማ ዞን የፍትህ ጽ/ቤት**
**የማስረጃዎች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ የስራ ሂደት**

በአዳማ ከተማ ዞን የፍትህ ጽ/ቤት
ለማስረጃዎች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ የስራ ሂደት
አዳማ

ቀን፡ 19/03/2007 ዓ.ም

**የውክልና ስልጣን ማስረጃ**

ወካዮች፡ 1. አቶ ተስፋዬ ረታ ተሊላ
2. ወ/ሮ ወርቅነሽ ደስታ
አድራሻ፡ አርሲ ዞን

ተወካይ፡ አቶ ብርሃኑ አሰፋ መሐሪ
አድራሻ፡ አዳማ ከተማ፣ ቀበሌ 01፣ የቤት ቁ. 2799

እኛ ወካዮች ህጋዊ ባልና ሚስት ስንሆን ለተወካይ የምንሰጣቸው የውክልና ስልጣን በ1ኛ ወካይ አቶ ተስፋዬ ረታ ተሊላ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን የሰሌዳ ቁጥሩ 3-49654AA፣ የሻንሲ ቁጥሩ JALK6A13X87101423፣ የሞተር ቁጥሩ 6HHL-435323 የሆነውን የደረቅ ጭነት ተሽከርካሪያችንን ተወካይ እንደ እኛ ሆነው እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲቆጣጠሩ፣ እንዲጠብቁ፣ እንዲያከራዩ፣ የኪራይ ገንዘብ እንዲቀበሉ፣ የተሽከርካሪውን ገቢ ተሳስበው እንዲቀበሉ፣ እንዲሸጡ፣ እንዲለውጡ፣ ስም እንዲያዘዋውሩ፣ ገንዘብ እንዲቀበሉ፣ ሰነድ እንዲሰጡና እንዲቀበሉ፣ ቦሎ ከላውዶ እንዲያስደርጉ፣ ግብርና አስፈላጊ ክፍያዎችን እንዲፈጽሙ፣ መዝገብ እንዲያንቀሳቅሱ፣ የኢንሹራንስ ውል እንዲገቡ፣ የንግድ ፈቃድ እንዲያወጡ፣ እንዲያሳድሱ፣ እንዲመልሱ፣ ሾፌር እንዲቀጥሩ፣ እንዲያሰናብቱ፣ ዲስፓች እንዲቀበሉ፣ ቼክ እንዲመነዝሩ፣ እኛ መፈጸም የሚገባንን ጉዳይ ሁሉ በማናቸውም መንግስታዊ፣ ህዝባውያን ድርጅቶች፣ ቀበሌ እና መንገድ ትራንስፖርት መ/ቤት ቀርበው ጉዳይ እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ፣ ሌላ 3ኛ ወገን ወይም የህግ ጠበቃ መወከልና መሻር እንዲችሉ ይህንን ሙሉ ውክልና ስልጣን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2199፣ 2204 እና 2205 መሰረት የሰጠናቸው መሆናችንን በፊርማችን እናረጋግጣለን፡፡

**የወካዮች ስምና ፊርማ**

1. ተስፋዬ ረታ ተሊላ - ተፈርሟል
2. ወርቅነሽ ደስታ - ተፈርሟል

**ማህተም**
በአዳማ ከተማ ዞን የፍትህ ጽ/ቤት
የማስረጃዎች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ የስራ ሂደት
አዳማ
ቁጥር 4428/1/07
በጽ/ቤታችን ቀርበው ፈርመዋል
ቀን፡ 01/04/2007 ዓ.ም
መሠረት ቲክሴ ቱቼ - ተፈርሟል
የዞን ዐቃቤ ህግ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. 3
Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 3

**ማህተም**
በአዳማ ከተማ ዞን የፍትህ ጽ/ቤት
የማስረጃዎች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ የስራ ሂደት

ስታዲየም የትርጉም ሥራ አገልግሎት
0930 098302
0911 662917
Stadium Translation Service

K.A. December 12, 2014

0|109| 2162
26/12/07

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
የዐቃቤ ህግ ቢሮ የህግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት
Prosecution Office Legal Advice and Opinion Directorate
የህግ ምክርና አስተያየት ማስታወሻ
Memorandum of Legal Advice and Opinion

ለ፡ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ

ቀን፡25/12/07

ከ፡ ሕግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት

ቁጥር፡ ሕ/ም/አ/ዳ/244/07

የህግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ም/ዋና ዐቃቤ ህግ

ጉዳዩ፡- የኮንትሮባንድ ዕቃ በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚሰጡ የውርስ ውሳኔዎችን በተመለከተ

በጉምሩክ አዋጅ አንቀጽ 153 (2) (ለ) መሠረት ባለሥልጣኑ ውሳኔ ከሚሰጥበት አቤቱታ መካከል አንዱ በማጓጓዣ ላይ በሚሰጥ የውርስ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ መሆኑ ተጠቅሶ ነገር ግን በአዋጁ አንቀጽ 147 (3) (ለ) መሠረት በሚሰጡ አብዛኞቹ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ የሚያቀርቡ የተሽከርካሪ ባለንብረቶች ተሽከርካሪውን የሚያስተዳድረው ወኪል በመሆኑ የድርጊቱን መፈፀም እነርሱ እንደማያውቁ ወይም ሊያውቁ እንደማይችሉ እንዲሁም በአዲሱ አዋጅ ላይ ባለቤት ወኪልን ይጨምራል የሚል ድንጋጌ የሌለ መሆኑን በመግለጽ ተሽከርካሪያቸው ሊወረስ እንደማይገባ እየተከራከሩ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 147 (3) (ለ) መሠረት የውርስ ውሳኔ ለማስተላለፍ የድርጊቱን መፈፀም ወኪሉ እንደሚያውቅ ማረጋገጥ በቂ ስለመሆኑ ወይም የባለቤቱን እውቀት ማረጋገጥ አስፈላጊ ስለመሆኑ የህግ አስተያየት እንዲሰጥበት ጥይቄ ቀርቧል፡፡

በዚህም መሠረት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 147 አፈጻጸም እንዲሁም በተደጋጋሚ የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭነው በሚያዙ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚወሰደውን እርምጃና የተሽከርካሪው ባለቤት በድርጊቱ ተሳትፎ እንዳለው የሚረጋገጥበትን ሁኔታ በተመለከተ በተለያዩ ጊዜያት ጥያቄ ቀርቦ በቁጥር 5.2.1/20/07 በቀን 21/06/07 ለአዋሳ ቅ/ጽ/ቤት እንዲሁም የጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ላቀረበው ጥያቄ በቁጥር ሕ/ም/አ/ዳ/130/07 በቀን 11/07/07 ለዐቃቤ ሕግ ቢሮ እንዲሁም በቁጥር 5.2.1/46/07 በቀን 27/10/07 በድጋሚ ለአዋሳ ቅ/ጽ/ቤት የተሰጠውን የሕግ አስተያየት በድምሩ 10 ገጽ አባሪ አድርገን የላክን ሲሆን የተሽከርካሪው ባለቤት ተወካይን የሚጨምር መሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 143 (4) እና 147 (3) (ሐ) አገላለጽ መረዳት የሚቻል ስለሆነ በአንቀጽ 147 (3) (ለ) የተቀመጠው ድንጋጌም በወኪሉ ላይ ተፈፃሚነት ሊኖረው ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. 2
Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

ህጉ በዚህ መልኩ ካልተተረጐመ የማጓጓዥያው "ባለቤት ወይም ኃላፊ የሆነ ሰው" በማለት በአንቀጽ 143 (4) እና 147 (3) (ሐ) የተመለከቱት ድንጋጌዎች ትርጉም የሚኖራቸው አይሆንም። ምክንያቱም ህጉ ወኪልን "ኃላፊ የሆነ ሰው" በሚለው መሠረት እንደባለቤት የማይቆጥረው ቢሆን ኖሮ በማስታወቂያ እንዲጠራ ያደርግ የነበረው ባለቤቱን ብቻ ይሆን ነበር።

በዚህ ምክንያት ማጓጓዥያውን የሚያስተዳድረው ወኪሉ በሚሆንበት ጊዜ ወኪሉ እንደ ባለቤት ተቆጥሮ "ኃላፊነቱን ይወስዳል"። በአዋጁ አንቀጽ 143 (4) "ኃላፊነቱን የሚወስድ ሰው" የሚለው ቃል የሚያሳየው ተሽከርካሪው የሚወረስ ሆኖ ከተገኘ ወኪሉ ኃላፊነት የሚወስድ መሆኑን ነው። ህጉ በዚህ መንገድ የማይተረጐም ከሆነ ወኪሉ በተሽከርካሪው የኮንትሮባንድ ንግድ እንዲያካሂድበት የመፍቀድ ያህል ይሆናል። ይህ እንዳይሆን ወኪሉ ተሽከርካሪው የኮንትሮባንድ ዕቃ መጫኑን እንደሚያውቅ የሚያመላክቱ ቀጥተኛ ማስረጃዎች (direct evidences) ወይም ከባቢያዊ ማስረጃዎች (circumstancial evidences) ከተገኙ ወኪሉ ለተፈፀመው ወንጀል ተጠያቂ ከመሆኑም በተጨማሪ ራሱ በፈፀመው ጥፋት የተነሣ ተሽከርካሪው ሊወረስ ይገባዋል ማለት እንደሆነ ግንዛቤ መያዝ አለበት።

ከወንጀል ኃላፊነት በስተቀር የፍትሐብሄር ባህሪ ያላቸውን አስተዳደራዊ ጥፋቶች ጨምሮ ማንኛውም በወኪሉ የተፈፀመ ድርጊት በወካዩ እንደተፈፀመ ስለሚቆጠር በወኪሉ ጥፋት ምክንያት የሚመጣ ኃላፊነት ሁሉ የወካዩ (principal) ኃላፊነት ጭምር መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል። ወኪሉ ከተሽከርካሪው ባለቤት የሚቀበለው ውክልና ለባለቤቱ በህግ በተሰጠው መብትና ሥልጣን እንዲሠራበት ብቻ ሳይሆን ህግ በራሱና በባለቤቱ ላይ የሚጥላቸውን የፍትሐብሄርና አስተዳደራዊ ኃላፊነቶች ጭምሮ እንዲወጣ የሚያስገድድ ሰነድ በመሆኑ አንድን ተሽከርካሪ እንዲያስተዳድር የተወከለ ሰው ተሽከርካሪው የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ በተገኘ ጊዜና ወኪሉ ይህን ሁኔታ ያውቃል የሚያሰኝ ሁኔታ መኖሩ በተረጋገጠ ጊዜ በወኪሉ ኃላፊነት ተሽከርካሪው መወረስ ይኖርበታል። በዚህ ጊዜ የተሽከርካሪው ባለቤት መብቱን የሚጠይቀው ከወኪሉ ብቻ ይሆናል ማለት ነው።

በሌላ በኩል ምንም እንኳን ሀገራችን የስምምነቱ ፈራሚ አካል ባትሆንም በዓለምአቀፍ ደረጃ የጉምሩክ አሠራርን ለማቀላጠፍ እና ወጥ ለማድረግ ተግባራዊ የተደረገው የተሻሻለው የኪዮቶ ስምምነት ሀገራት ወጥ የሆነ አሠራርን ለመተግበር እንዲረዳቸው ካካተታቸው ልዩ አባሪዎች መካከል ስለጉምሩክ ወንጀሎች በሚያወራው specific annex H ቁጥር 16 ላይ

> "Means of transport should be fortified or confiscated where the owner, operator or person in charge was, at the time, a consenting party or privy to the customs offence or has not taken all reasonable steps to prevent the commission of the offence..."

በማለት በማጓጓዣው ላይ ኃላፊ የሆነ ሰው ወይም ወኪሉ በወንጀሉ ባለው ተሳትፎ ምክንያት ተሽከርካሪው ሊወረስ እንደሚችል ያመለክታል።

በመሆኑም የተሽከርካሪው ወኪል የወንጀል ድርጊቱን እያወቀ የድርጊቱን መፈፀም ለመከላከል ወይም ለማስቀም ተገቢውን እርምጃ ሳይወስድ መቅረቱ እስከተረጋገጠ ድረስ ተሽከርካሪው እንዲወረስ ቢደረግ ተገቢ ነው በማለት አስተያየታችንን እናቀርባለን።

ከሠላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 1

S.ጸ/ዐ/1/46/07

27 ሰኔ 2007

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ለአዋሳ ቅ/ጽ/ቤት

<u>አዋሳ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የተሽከርካሪ ውርስን በተመለከተ የቀረበ ጥያቄ</u>

<u>የጉዳዩ ፍሬ ነገር</u>

አቶ ደጀኔ ጥበቡ የተባሉ ግለሰብ ንብረት የሆነ ታርጋ ቁጥሩ ኮድ 3-90552 ተሽከርካሪ በ2006 ዓ.ም የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ መያዙና አስተዳደራዊ ቅጣት ተቀጥቶ መውጣቱን እንዲሁም የዚህ ግለሰብ ንብረት የሆነ ታርጋ ቁጥሩ ኮድ 3-85234 አ.አ የሆነ ሌላ ተሽከርካሪ ደግሞ በ2005 እና 2006 ዓ.ም በ3 የተለያዩ ጊዜያት የኮንትሮባንድ እቃ ጭኖ በቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ አስተዳደራዊ ቅጣት ተቀጥቶ መለቀቁን ገልፃችሁ ነገር ግን ይህ ተሽከርካሪ በድጋሚ ታህሳስ 9 ቀን 2007 ዓ.ም ህገ-ወጥ ዕቃ ጭኖ በመገኘቱ በቅ/ጽ/ቤቶች ተይዞ የሚገኝ መሆኑን በመጥቀስ ተሽከርካሪው ለ4ኛ ጊዜ ጥፋት ፈጽሞ በመገኘቱ በመመሪያ ቁጥር 50/2003 መሠረት መዝገቡ ተጣርቶ በዐቃቤ ህግ በኩል ክስ ሊመሰረትበት የሚገባ መሆኑን ወይም ወንጀል የተፈፀመው አዲሱ አዋጅ ከወጣ በኋላ በመሆኑ የተሽከርካሪውን ባለቤት ተሳትፎ ወይም እውቀት በማስረጃ ማረጋገጥ ባይቻልም የወንጀሉን ተደጋጋሚነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በአዋጁ አንቀጽ 147(3)(ለ) መሠረት ሊወረስ የሚገባ ስለመሆኑ አስተያየት እንዲሰጥበት ተጠይቋል፡፡

<u>የጉዳዩ ጭብጥ</u>

- በተደጋጋሚ ህገ-ወጥ ዕቃ ጭኖ የተያዘ እና በቅጣት የተስተናገደ ተሽከርካሪ ባለቤት በጉዳዩ ላይ ያለውን ተሳትፎ በማስረጃ ሊረጋገጥ ባልቻለበት ሁኔታ ተሽከርካሪው ላይ የሚወሰደው እርምጃ ምንድን ነው?

<u>አግባብነት ያለው ህግ</u>

- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 147(3)

የህግ አስተያየት

በጉምሩክ አዋጁ አንቀጽ 147(3) መሠረት ህገ-ወጥ እቃዎችን ሲያጓጉዙ የሚያዙ ተሽከርካሪዎች ውርስ የሚደረጉባቸው ሁኔታዎች ተለይተው የተመለከቱ ሲሆን በዚህ መሠረት ማጓጓዣው እቃዎችን ለመደበቅ እንዲያስችል ሆኖ ከተሰራ፣የማጓጓዣ ባለቤቱ እያወቀ የድርጊቱን መፈፀም ለመከላከል ወይም ለማስቆም ተገቢውን እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ ወይም የንብረቱ ባለቤት ወይም ሀላፊ የሆነ ሰው በማስታወቂያ ተጠርቶ በተገቢው ጊዜ ያልቀረበ እንደሆነ ተሽከርካሪው ውርስ እንደሚደረግ ተደንግጓል፡፡

አስተያየት በተጠየቀበት ጉዳይ ላይም ተሽከርካሪው አዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በተለያየ ጊዜ ለፈፀመው ጥፋት በመመሪያ ቁጥር 50/03 መሠረት ተገቢውን ቅጣት ከፍሎ መለቀቁ የተገለፀ ሲሆን ነገር ግን ለ4ኛ ጊዜ ጥፋቱ የተፈፀመው አዲሱ የጉምሩክ አዋጅ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ሲሆን በዚህ አዋጅ መሠረት ህገ-ወጥ እቃ በጫኑ ማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ የሚጣል አስተዳደራዊ ቅጣት የሌለ በመሆኑና መመሪያ ቁጥር 50/03 ተፈፃሚነቱ ቀሪ በመደረጉ ጥፋቱ ለ4ኛ ጊዜ ቢፈፀምም እንኳን ጉዳዩ በአዲሱ አዋጅ መሠረት የሚስተናገድ እንጂ በቀድሞው መመሪያ መሠረት ምርመራ ተጣርቶ ክስ የሚመሠረትበት ሁኔታ የለም፡፡

በመሆኑም ጥያቄ ለቀረበበት ጉዳይ አግባብነት ያለው ህግ አዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 በመሆኑ ጉዳዩ በአዋጁ መሠረት ሊስተናገድ የሚገባ ሲሆን በአዲሱ አዋጅ መሠረት አንድ ማጓጓዣ የሚወረሰው በምን ሁኔታ እንደሆነ ከዚህ ቀደም በተለያየ ጊዜ በጉዳዩ ላይ ዝርዝር አስተያየት የሰጠን በመሆኑ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ጉዳዩን በመመርመር ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ያለባችሁ መሆኑን እየገለጽን የተሰጡትን አስተያየቶች ፬ ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልፃለን፡፡

በኢትዮጵያ ... ምታ ጋር
... የህግ ... ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር
... ህግ

ግልባጭ

- ለዐቃቤ ህግ ቢሮ

  ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. 2
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

ለ፡ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ 17/10/07

ቀን፡17/10/07

ከ፡ ሕግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት

ቁጥር፡ ሕ/ም/አ/ዳ/195/07

ጉዳዩ፡- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 147(3) አፈጻጸም በተመለከተ

የአቶ ሙኽዲን ሁሴን አብዲ ንብረት የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-01379 ድሬ የሆነ ተሽከርካሪ ከፍተኛ መጠን ያለው የኮንትሮባንድ ዕቃ ተጭኖበት ጫካ ውስጥ ሲንቀሳስ በቀን 01/06/07 ዓ.ም. መያዙን እንዲሁም የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-03135 ድሬ የሆነ ተሽከርካሪ ግምቱ 406,176 ብር የሆነ ሙሉ በሙሉ የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ ሲያጓጉዝ መያዙን በተጨማሪም የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-01184 ድሬ የሆነ ተሽከርካሪም በተመሳሳይ ሁኔታ ግምቱ 330,876 ብር የሚሆን የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ መያዙን በመግለጽ በተሽከርካሪዎቹ ላይ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 147(3) (ሀ) እና (ለ) መሠረት የውርስ ውሳኔ ለመስጠት ስላልተቻለ ጉዳዩ በጥልቀት ታይቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት በቁጥር 12.1/01-16/1229 በቀን 18/09/07 እና 12.1/01.16/1242 በቀን 24/09/2007 በተጻፉ ደብዳቤዎች ጥያቄ ቀርቧል፡፡

በዚህም መሠረት በተመሳሳይ ሁኔታ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 147(3) አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭነው የተያዙ ተሽከርካሪ ባለቤቶች በድርጊቱ ተሳትፎ እንዳላቸው የሚረጋገጥበትን ሁኔታ እና የውርስ ውሳኔ የሚሰጠውን አካል በተመለከተ ጥያቄ ቀርቦ በቁጥር 5.2.1/20/07 በቀን 21/06/2007 ለአዋሳ ቅ/ጽ/ቤት የተሰጠ አስተያየት እንዲሁም የጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ላቀረበው ጥያቄ በቁጥር ሕ/ም/አ/ዳ/130/07 በቀን 11/07/07 ለዐቃቤ ሕግ ቢሮ የተላከውን አስተያየት በድምሩ 7 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን ሲሆን እነዚህን የሕግ አስተያቶች መሠረት በማድረግ የቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ጥያቄ ለቀረበባቸው ጉዳዮች ተገቢውን ውሳኔ መስጠት እንደሚችል እየገለጽን በተጨማሪም ከውርስ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ተሽከርካሪዎቹ ኮንትሮባንድ ዕቃ የጫኑት ሲሄዱ ነው ወይስ ሲመለሱ? ህጋዊ ዕቃ በተጨማሪነት ጭነዋል ወይስ አልጫኑም? የመኪና ኪራይ ለባለቤቱ ተከፍሏል ወይስ አልተከፈለም? የሚሉት ቢያንስ መጣራት አለባቸው፡፡ ተሽከርካሪዎቹ የጫኑት ሲሄዱ ከሆነ የስምሪቱ መነሻ የባለንብረቱ ትዕዛዝና ፈቃድ ከመሆኑም በላይ ጭነቱን የማስማራት፣ዋጋ የመደራደርና የመወሰን፣ገንዘቡን (ኪራዩን) የመቀበል፣ስምሪቱን የመቆጣጠርና የመከታተል (ተሽከርካሪውን የማስተዳዳርና እንቅስቃሴውን በተለይም ጭኖ ሲወጣ የመቆጣጠር) ሥልጣንና መብት ያለው ባለቤቱ ስለሆነ በዚህ መብቱ ሲሠራበት ስለተጫነው ዕቃ አያውቅም ተብሎ አይገመትም፡፡ ስለዚህ ይህን ከግምት በማስገባት ሥራ አስኪያጁ የራሱን ውሳኔ መወሰን ይችላል በማለት አስተያየታችንን ...

ከሰላምታ ጋር

5-2-1/20/07
21 የካቲት 2007

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ለአዋሳ ቅ/ጽ/ቤት

<u>አዋሳ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭነው የተያዙ ተሽከርካሪ ባለቤቶች በድርጊቱ ተሳትፎ እንዳላቸው የሚረጋገጥበትን ሁኔታ እና የውርስ ውሳኔ የሚሰጠውን አካል በተመለከተ</u>

<u>የጉዳዩ ፍሬ ነገር</u>

በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 147 መሠረት ህገ-ወጥ ዕቃን ለማጓጓዝ የዋለ ተሽከርካሪ ባለቤት ድርጊቱን እያወቀ ለመከላከል ወይም ለማስቆም ተገቢውን እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ ተሽከርካሪውን እንደሚወርስ ቢደነግግም፡-

- ሙሉ ኮንትሮባንድ ዕቃ የጫነ ተሽከርካሪን በተመለከተ ተሽከርካሪውን ለመውረስ ባለቤቱ ስለጉዳዩ ያለውን እውቀት በማስረጃ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ፤
- ተሽከርካሪው የሚወረስ ወይም የሚለቀቅ ከሆነ ይህ ውሳኔ በየትኛው የስራ ክፍል እንደሚወሰን፤እንዲሁም
- የተሽከርካሪው ባለቤት ተቃውሞ የሚያቀርበው ለማን እንደሆነ፤

የህግ አስተያየት እንዲሰጥበት ጥያቄ ቀርቧል፡፡

<u>የጉዳዩ ጭብጥ</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጸ 147 መሠረት በማጓጓዣ ላይ የውረስ ውሳኔ ለመስጠት

- የተሽከርካሪው ባለቤት ስለድርጊቱ እውቀት እንዳለው እንዴት ይረጋገጣል?
- ተሽከርካሪውን የመውረስ ወይም የመልቀቅ ውሳኔ በማን ይሰጣል?
- የተሽከርካሪው ባለቤት ተቃውሞውን ለየትኛው አካል ማቅረብ አለበት?

<u>አግባብነት ያለው ህግ</u>

- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000
- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 147 አንቀጽ 153(2)(ለ)

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

## የህግ አስተያየት

በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ መሠረት የሚወረሱ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የዋለ ማጓጓዣ የሚወረስባቸው ሁኔታዎች በአዋጁ አንቀጽ 147(3) ላይ በዝርዝር የተመለከቱ ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) ላይ የማጓጓዣው ባለቤት እያወቀ የድርጊቱን መፈፀም ለመከላከል ወይም ለማስቆም ተገቢውን እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ ማጓጓዣው የሚወረስ መሆኑ ተመልክቷል። በመሆኑም አንድ የማጓጓዣ ባለቤት ስለድርጊቱ እውቀት አለው የሚባለው መቼ ነው የሚለውን ለመመለስ ጉዳዩ በምርመራ ክፍሉ በኩል በሚደረግ ማጣራት የሚወሰን ይሆናል። ነገር ግን አንዳንድ ሁኔታዎችን ለመጠቆም ያህል ለምሳሌ በቀድሞው አዋጅ መሠረት ህገ-ወጥ ዕቃዎችን በሚያጓጉዙ የማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ በወጣው መመሪያ ቁጥር 50/2003 አንቀጽ 4 ላይ የምርመራ ቡድኑ ባለቤቱ የወንጀል ተሳትፎ እንደሌለው ለማረጋገጥ በአንቀፁ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በማጣራት በወንጀል ተሳትፎ የነበረው መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ እንደሚችል ያመለክታል።

በሌላ በኩል ተሽከርካሪው ዕቃ ወደሚወስድበት አካባቢ በባለቤቱ ስምሪት ምንም ሳይጭን ባዶውን ተጉዞ የነበረ መሆኑ፣ባለቤቱ ለተጫነው ህገ-ወጥ ዕቃ የመኪና ኪራይ መቀበሉ፣ከኢትዮጵያ ቴሌኮሚዩኒኬሽን ኮርፖሬሽን በሚገኝ መረጃ መሠረት ባለቤትና የኮንትሮባንድ ተግባሩን የሚፈጽመው ሰው የስልክ ግንኙነት ማድረጋቸው  የመሳሰሉ ተግባራት የባለቤቱን እውቀት ለማስረዳት ልናጣራቸው እና በምርመራ ልንደርስባቸው የሚቻሉ ሁኔታዎች ናቸው። በመሆኑም አንድ ተሽከርካሪ ላይ ሙሉ የኮንትሮባንድ ዕቃ መጫኑ ባለቤቱ ድርጊቱን ያውቀው ነበር ለማለት ጠቋሚ ቢሆንም ነገር ግን ይህ ሁኔታ በሌሎች ማስረጃዎች የተደገፈ ሊሆን ይገባል።

በሁለተኛነት የቀረበውን ተሽከርካሪውን የመውረስ ወይም የመልቀቅ ውሳኔ የሚሰጠውን የስራ ክፍል በተመለከተም በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 8 መሠረት የባለሥልጣኑን ሥልጣን እና ተግባራት የማስፈፀም ስልጣን ለዋና ዳይሬክተሩ እንደተሰጠ ተደንግጓል። በሌላ በኩል ሁሉም ተግባራት በዋና ዳይሬክተሩ ሊፈፀሙ የማይችሉ በመሆኑ በቀጥታ በአዋጁ ለዋና ዳይሬክተሩ ከተሰጡት ሀላፊነቶች ውጪ ሌላው በየቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስራ አስኪያጆች ተፈፃሚ የሚደረግ ነው። በመሆኑም የሰዎችን ንብረት ከመያዝ እና ከመልቀቅ ጋር በተያያዘ የሚሰጥ ውሳኔ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደረጃ ሲሆን በስራ አስኪያጁ ደረጃ ሊሰጥ የሚገባ ሲሆን ይህም ጉዳይ በህግ ማስከበር የሥራ ሂደት አስተባባሪ የውሳኔ ሀሳብ እየቀረበ በስራ አስኪያጅ ሊወሰን ወይም በቅ/ጽ/ቤቱ ማኔጅመንት ቃለ-ጉባኤ በመያዝ ተሽከርካሪዎች የመውረስ ወይም የመልቀቅ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል።

በሶስተኛነት የቀረበው ጥያቄ የተሽከርካሪው ባለቤት ያለውን ተቃውሞ ለማን ማቅረብ እንዳለበት የሚመለከት ሲሆን ይህም ጉዳይ በአዋጁ አንቀጽ 153 (2)(ለ) ላይ እንደተመለከተው በማጓጓዣው ውርስ ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በባለሥልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት በሚቋቋመው የአቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል እንደሚታዩ የተደነገገ በመሆኑ የተሽከርካሪው ባለቤት ተቃውሞ ካለው ቅሬታውን ለዚሁ አካል ማቅረብ ይችላል።

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

በመሆኑም በተነሱት ጉዳዮች ላይ ወጥ የሆነ አሠራር እንዲኖር የሚወረሱ ዕቃዎች እና ማጓጓዣዎችን የውርስ አፈፃፀም በተመለከተ መመሪያ እስኪዘጋጅ ድረስ ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ተፈፃሚ ሊደረግ ይገባል በማለት አስተያየታችንን እናቀርባለን።

ከሠላምታ ጋር

[illegible] አህመድ
የህግ ምክርና አስተያየት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር
ም/ዋና ዐቃቤ ህግ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

ግልባጭ

➢ ለዐቃቤ ህግ ቢሮ
<u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን</u>

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. ፪
Ethiopian Revenues and Customs Authority No. 2
Records & Documentation

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
የዐቃቤ ህግ ቢሮ የህግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት
Prosecution Office Legal Advice and Opinion Directorate
የህግ ምክርና አስተያየት ማስታወሻ
Memorandum of Legal Advice and Opinion

ለ፡ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ

ቀን፡11/07/07

ከ፡ ሕግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት

ቁጥር፡ ሕ/ም/አ/ዳ/130/07

ጉዳዩ፡- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 147(3) (ለ) አፈጻጸም በተመለከተ

የጉዳዩ ፍሬ ነገር

በጅ/ገ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት በተደረገው የፀረ-ኮንትሮባንድ የሕግ ማስከበር ሥራ ብዛት ያላቸው ተሽከርካሪዎች የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን ጭነው በቁጥጥር ስር ውለው የሚገኙ ሲሆን ውሳኔ ለመስጠት እንዲቻል በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 147(3) (ለ) ላይ በዋናው መሥሪያ ቤት በተሰጠ ሥልጠና የተሽከርካሪው ባለቤት ኮንትሮባንድ ስለመጫኑ እውቀት ካለው እና ድርጊቱን ለመከላከል ተገቢውን ጥንቃቄ ወይም እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ በማስረጃ ተረጋግጦ ተሽከርካሪው እንደሚወረስ ግልጽ ቢሆንም በሥልጠናው ወቅት ተሽከርካሪው ሙሉ ጭነት ወይም በከፊል ኮንትሮባንድ ጭኖ ከተያዘ የተሽከርካሪው ባለቤት ዕውቀት እንዳለው ስለሚገመት ተሽከርካሪው እንደሚወረስ ሥልጠና እንደተሰጠ ገልጻችሁ በአፈጻጸም ላይ ያጋጠማችሁን ችግሮች ስትገልፁ፣

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 147(3) (ለ) መሠረት ተሽከርካሪ ለመውረስ የተሽከርካሪው ባለቤት ስለተፈጸመው ወንጀል ዕውቀት አለው የሚባለው መቼ እንደሆነና የተሽከርካሪው ባለቤት ዕውቀት አለው ከተባለ ደግሞ በወንጀል ለማስቀጣት ወንጀልን ከሚያቋቁሙት ሶስት መሠረታዊ ክፍሎች መካከል ድርጊቱን ባለቤቱ ሲፈጽም ባለመያዙ መክሰስ መቻሉን በተመለከተ፣
- ተሽከርካሪው በሙሉ ወይም በከፊል የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን ጭኖ ከተያዘ የተሽከርካሪው ባለቤት ዕውቀት አለው ለማለት የሚያስችል ግልጽ የሕግ ግምት በሌለበት ሁኔታ ተሽከርካሪውን መውረስ መቻሉንና በሙሉ ወይም በከፊል የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን ጭኖ ከተያዘ ተሽከርካሪው ይወረሳል ከተባለ ደግሞ ሙሉ ጭነት ወይም በከፊል ጭነቱን ለማለት መነሻ የሚሆነው ምን እንደሆነ እንዲሁም መለኪያው ምን ሊሆን እንደሚገባ፣

Ethiopian Revenues and Customs Authority No. 2
Records & Documentation

- ማጓጓዣ እና ዕቃን የመውረስ ሥልጣን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 147(6) በባለሥልጣኑ በአስተዳደር እንዲወሰን የተሰጠ ሲሆን በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ የትኛው የሥራ ክፍል ሊወሰን እንሚገባ፣

የሕግ አስተያየት እንዲሰጥ ጥያቄ አቅርባችኋል፡፡

## የተያዘው ጭብጥ

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 147(3) (ለ) መሠረት ተሽከርካሪ ለመውረስ የተሽከርካሪው ባለቤት ስለተፈጸመው ወንጀል ዕውቀት አለው የሚባለው መቼ ነው? የተሽከርካሪው ባለቤት ስለወንጀሉ ዕውቀት እንዳለው ከተረጋገጠ በኋላ ድርጊቱን ሲፈጽም ካልተያዘ በወንጀል መክሰስ ይቻላል?
- ተሽከርካሪው በሙሉ ወይም በከፊል የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን ጭኖ ከተያዘ የተሽከርካሪው ባለቤት ዕውቀት አለው በሚል ተሽከርካሪው የሚወረሰው በምን የሕግ አግባብ ነው? ሙሉ ጭነት ወይም በከፊል ጭኗል ለማለት መነሻ የሚሆነው ምንድን ነው? መስኪያውስ?
- በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ የውርስ ውሳኔን የሚሰጠው የትኛው የሥራ ክፍል ነው?

## አግባብነት ያለው ሕግ

- ህገ-ወጥ ዕቃዎችን በሚያጓጉዙ የማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ በወጣው መመሪያ ቁጥር 50/2003 አንቀጽ 4
- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀጽ 8
- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 147
- የወንጀል ሕግ 32(1) (ለ) ናቸው፡፡

## የሕግ አስተያየት

በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ መሠረት የሚወረሱ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የዋለ ማጓጓዣ የሚወረስባቸው ሁኔታዎች በአዋጁ አንቀጽ 147(3) ላይ በዝርዝር የተመለከቱ ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) ላይ የማጓጓዣው ባለቤት እያወቀ የድርጊቱን መፈፀም ለመከላከል ወይም ለማስቆም ተገቢውን እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ ማጓጓዣው የሚወረስ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አንድ የማጓጓዣ ባለቤት ስለድርጊቱ እውቀት አለው የሚባለው መቼ ነው የሚለውን ለመመለስ ጉዳዩ በምርመራ ክፍሉ በኩል በሚደረግ ማጣራት የሚወሰን ይሆናል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ሁኔታዎችን ለመጠቆም ያህል ለምሳሌ በቀድሞው አዋጅ መሠረት ህገ-ወጥ ዕቃዎችን በሚያጓጉዙ የማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ በወጣው መመሪያ ቁጥር 50/2003 አንቀጽ 4 ላይ የምርመራ ቡድኑ ባለቤቱ የወንጀል ተሳታፊ እንደሆነው ለማረጋገጥ በአንቀፁ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በማጣራት በወንጀል ተሳታፊ የነበረ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ እንደሚችል ያመለክታል፡፡

Ethiopian Re... and Customs Authority
Record... Documentation No. 3

በሌላ በኩል ማጓጓዥያው ዕቃው ወደ ተጫነበት ቦታ ጭነት ሳይጭን የተጓዘ መሆኑንና ሙሉ ኮንትሮባንድ /የኮንትሮባንድ ጭነት ብቻ/ ጭኖ የተመለሰ መሆኑን፣ ጭነቱ ባለቤቱ ከሚኖርበት ወደ ሌላ ቦታ የሚጓጓዝ ከሆነ ማጓጓዥያው ሙሉ ኮንትሮባንድ ጭነት ጭኖ ከሚኖርበት አካባቢ የተነሳ መሆኑን፣ የማጓጓዥያው ባለቤት ለተጫነው ህገ-ወጥ ዕቃ የመኪና ኪራይ መቀበሉ፣ ከኢትዮጵያ ቴሌኮሚዩኒኬሽን ኮርፖሬሽን በሚገኝ መረጃ መሠረት ባለቤትና የኮንትሮባንድ ተግባሩን የሚፈጽመው ሰው ጋር ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊትም ሆነ በኋላ የስልክ ግንኙነት ወይም በማንኛውም መልኩ ያደረጉት ግንኙነቶች መኖራቸውን እና የመሳሰሉ ተግባራትን በመውሰድ የባለቤቱን እውቀት ለማስረዳት ልናጣራቸው እና በምርመራ ልንደርስባቸው የሚቻሉ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ በስልጠናው ለማስጨበጥ የተፈለገውም እነዚህን የመሣሠሉ የምርመራ ቴክኒኮች መከናወን ያለባቸው መሆኑን እንጂ ሙሉ የኮንትሮባንድ ጭነት የጫኑ ተሽከርካሪዎች ሁል ጊዜ ይወረሳሉ ለማለት አይደለም፡፡

በመሆኑም በአንድ ተሽከርካሪ ላይ ሙሉ ወይም በከፊል የኮንትሮባንድ ዕቃ ብቻ መጫኑ ባለቤቱ ተሽከርካሪውን የሚያስተዳድር፣የሚከታተልና የሚቆጣጠር፣ጭነት የሚያፈላልግና ዋጋ የሚደራደር እንደመሆኑ መጠን ድርጊቱን ያውቀው ነበር ለማለት ጠቋሚ ቢሆንም የማጓጓዣ ባለቤቱ ስለተፈጸመው ወንጀል ዕውቀት ነበረው ለማለትና ማጓጓዣውን ለመውረስ ግን ይህ ሁኔታ በሌሎች ማስረጃዎች የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡ ማለትም አንድ ተሽከርካሪ በሙሉ ወይም በከፊል የኮንትሮባንድ ዕቃ ብቻ ጭኖ መያዙ ብቻውን ባለቤቱ ስለወንጀሉ ዕውቀት አለው ለማለት በቂ ማስረጃ ስለማይሆን ማጓጓዣውን ለመውረስም ሆነ የወንጀል ክስ ለመመስረት የሚያስችሉ ሌሎች ማስረጃዎችን ማሰባሰብ ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ የባለቤቱን የወንጀል ተሳታፊነት ለማረጋገጥ በሙሉ ወይም በከፊል ኮንትሮባንድ ብቻ መጫኑን ከመለካት ባለፈ የወንጀል ክስ ለመመስረት የሚያስችሉ ማስረጃዎችን ማግኘት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ ይህ ደግሞ የህግ ጥያቄ ሳይሆን የምርመራ ብቃትንና የቴክኒክ ጥያቄዎችን የሚመለከት በመሆኑ በጥንቃቄ ሊሠራበት ይገባል፡፡

በሌላ በኩል የማጓጓዣው ባለቤት ስለወንጀሉ ዕውቀት እንዳለው በበቂ ማስረጃ ከተረጋገጠ በኋላ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 መሠረት ወንጀልን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ስለሆኑ ባለቤቱ ደግሞ ድርጊቱን ራሱ ሲፈጽም ስላልተያዘ በወንጀል ተጠያቂ የሚደረግበትን አግባብ በተመለከተ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1) (ለ) ማንም ሰው ወንጀሉን እርሱ ራሱ በቀጥታ ባያደርግም እንኳን በመላ ሃሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ ሲሆን በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንደፈጸመ ተቆጥሮ እንደሚቀጣ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ በመነሳት የማጓጓዣው ባለቤት ምንም እንኳን በቀጥታ በወንጀሉ ውስጥ ተሳታፊነት ባይኖረውም በወንጀል ድርጊቱ ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ወይም ተጠቃሚ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ መሆኑን በማጣራት የወንጀል ክስ ሊመሰረትበት ይችላል፡፡

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

በሶስተኛነት የቀረበው ተሽከርካሪውን የመውረስ ወይም የመልቀቅ ውሳኔ የሚሰጠውን የስራ ክፍል በተመለከተም በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 8 መሠረት የባለሥልጣኑን ሥልጣን እና ተግባራት የማስፈፀም ስልጣን ለዋና ዳይሬክተሩ እንደተሰጠ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል ሁሉም ተግባራት በዋና ዳይሬክተሩ ሊፈፀሙ የማይችሉ በመሆኑ በቀጥታ በአዋጁ ለዋና ዳይሬክተሩ ከተሰጡት ኃላፊነቶች በስተቀር ለባለሥልጣኑ የተሰጡ ሥልጣንና ኃላፊነቶች በቅርንጫፍ ደረጃ ሲሆን ለተለየ የሥራ ክፍል ካልተሰጡ በስተቀር በየቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስራ አስኪያጆች ተፈፃሚ የሚደረጉ ናቸው፡፡ በመሆኑም የሰዎችን ንብረት ከመያዝ እና ከመልቀቅ ጋር በተያያዘ የሚሰጥ ውሳኔ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደረጃ በመሆኑና ለሌላ የሥራ ክፍል ተለይቶ ያልተሰጠ ስለሆነ ውሳኔው በቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ደረጃ ሊሰጥ የሚገባ ሲሆን ይህም ጉዳይ በሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት አስተባባሪ የውሳኔ ሀሳብ እየቀረበ በስራ አስኪያጅ ሊወሰን ወይም በቅ/ጽ/ቤቱ ማኔጅመንት ቃለ-ጉባኤ በመያዝ ተሽከርካሪዎች የመውረስ ወይም የመልቀቅ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት የቅጣትና የውርስ አፈፃፀም መመሪያ በቅርቡ ፀድቆ የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

በመሆኑም በተነሱት ጉዳዮች ላይ ወጥ የሆነ አሠራር እንዲኖር የሚወረሱ ዕቃዎች እና ማጓጓዣዎችን የውርስ አፈፃፀም በተመለከተ መመሪያው እስኪፀድቅ ድረስ ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ተፈፃሚ ሊደረግ ይገባል በማለት አስተያየታችንን እናቀርባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ቤተ መዛግብትና ዶኩመንቴሽን ቁ. 1
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 1